Abay gidib

# የአባይ ግድብ፦
# መልሚያችን ወይስ መበታተኛችን?!

### በኮማንደር አሰፋ ሰይፉ

ሚያዝያ ፪ሺህ ፫

( ልዩ ማሳሰቢያ! እባካችሁ የአገር ተረካቢ ወጣቶች እንዲያውቁ አድርጉ! )

አጭር ታሪካዊ መግቢያ፦

እንደ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክኸርስት፦በጥንት ጊዜ ፲፯/፲፰ (ጥርጣሬው የእኔ) ኢትዮጵያውያን ፈርኦኖች ግብጽን አስተዳድረዋል። ፍራንክ ኤም ስኖውደን ጁኒየር ደግሞ ፳፭ ያደርሷቸዋል። ሊረሳ የማይገባው የኢትዮጵያ ነገሥታት ግብጻውያን በክርስቲያን ወንድሞቻቸው ላይ ግፍ ሲፈጽሙባቸው ያስቆሙ እንደነበረም ነው።
ከዚያም በኋላ ግብጻውያን በግሪኮች፦በሮማውያንና፦በቱርኮች እንዲሁም በእንግሊዞች ተገዝተዋል።
አባይን በተመለከተ ችግር የተጀመረብን በእንግሊዞች ነው።እንግሊዞች ገደብ ለሌለሽ ዘመን ግብጽንና ሱዳንን እንዲሁም በዙሪያችን ያሉትን የሚገዙ መስሏቸው፦ ያደረሱብን ችግሮች አያሌ ናቸው። ጠንቆቹ አልለቀቁንም! እንለፋቸው! ኢትዮጵያ አንድ ቀን አባይን ብትገድብ፦ ወይም እገድባለሁ ብላ ብታስፈራራ በግዛቶችዋ፦ ግብጽና ሱዳን፦ ላይ ጠንካራ ተጽዕኖ ልታሳድር መቻልዋን በመገንዘብ እንግሊዝ መላ መምታት ጀመረች።
አማራጮችዋም፦ ብትችል ግዛትዋን አባይ ምንጭ ድረስ ማስፋፋት ባትችል ኢትዮጵያን በውል ማሰር ነበር።ኹለተኛው ላይ ስናተኩር አጼ ምኒልክን ብትሞክር፦ የእምዬ ምኒልክ ቁርጥ ያለው መልስ ‘ ኢትዮጵያ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላት አገር ናት። ማንም በውሀ ጥም እንዲሞት አትፈልግም። ስለዚህ የአባይን ወንዝ አታቋርጠውም።’ ሲሉ፣ የኢትዮጵያችንን በወንዟ ላይ የማብዛት የመቀነስ መብቷን ሳያስደፍሩ፦ ተጽዕኖውን ኹሉ ተቋቁመው ነው የተዋዋሉት።

በልጅ ኢያሱ ጊዜ፦ ሞግዚታቸውን፦ ራስ ተሰማን ቢሞክሯቸው ኹሉንም ሰምተው እጅ ከመንሳት በስተቀር(ለፈረንጆቹ ኹሉ) ምንም ዓይነት መልስ ባለመስጠታቸው ምድረ-ፈረንጅን ግራ አጋብተው ነበር።

ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ( ቀኃሥ) ስንመጣ፦ በቀድሞዎቹ ላይ የነበሩትን ተጽዕኖዎች ኹሉ እንደተሸከሙ፦ ርሳቸውንም ቢሞክሩ አልተበገሩላቸውም። ናስር አስዋንን በሶቪየቶች ሲያስገድብ ቀ.ኃሥ አሜሪካኖችን በቅጽበት ጠይቀው በመላ አገራችን ላይ ሰፊ የግድብና የመስኖ ጥናቶችን አስጠኑ። ለማስገደብም ሲዘጋጁ አሜሪካን ግብጽን ከሶቪየቶች እጅ ለማውጣት ዕድል ስላገኘች ሳይሳካ ቀረ። በዚያን ወቅት በፈረንጆች ኖቬምበር 57 ጥቅምት ፳፫ ምክር ቤቱን ሲከፍቱ ካሉት ውስጥ በትርጉም ትንሽ ላቃምስ።
“ የአባይ ወንዝ ውሀ ለኹለታችንም አገሮች ውድ ሕዝቦች ለሕይወትና ላስፈላጊ ነገሮች ኹሉ እንዲውሉ ማድረግ ላለንበት ዘመን ብቻ ሳይኾን ለሚቀጥሉት ምዕተ-ዓመታትም ነው። ይኽም ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ሲኾን ችግሩም የዚያኑ ያህል እጅግ ከባድ ነው።ኾኖም በእንዲህ ዓይነት ለጋስነት ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የሰጣትን ታላቅ ሃብት ለወዳጅ ጎረቤት አገሮች ስታካፍል፦ **ቀደምት ኃላፊነትዋና የተቀደሰው ግዳጅዋ በፍጥነት ማደግ ላይ ላለው ሕዝቧ ዕድገትና ብልጽግና ነው።**
(ከንግሊዝኛ የተተረጎመ ሲኾን ትርጉሜ ለራሴው ስላልጣፈጠኝ እንግሊዝኛው እነሆ)
*Nov. 12, 1957*
*“ It is a of a paramount importance to Ethiopia and a problem of the first order that the waters of the Nile be made to serve both of our beloved people now living and those that follow us in the centuries to come.*
*However generously Ethiopia may be prepared to share this tremendous God given wealth of hers with friendly neighbouring countries for the life and welfare of their people it is Ethiopia’s primary sacred duty to devote her water resources in the interest of her own rapidly expanding population and economy.”*

*እስቲ በግል ከክ. ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት ስለዚህ የተማርሁትን ልጨምርላችሁ። ለቀኃሥ ይህ ጉዳይ ምን ያህል አሳሳቢ እንደነበር ይገልጻልና! እጅግ በመደነቅ ጃንሆይ ዛሬ አባይን በተመለከተ ለጥቂቶቻችን የነገሩን ነገር እጅግ ይገርማል ብለው፦*
*" አባይ የዛሬው ትውልድ ብቻ ሳይኾን የምንጊዜውም ተከታታይ ትውልድ ሃብት ስለኾነ* ***<u>ማንም ሰው በሚቀጥሉት የኢትዮጵያ ትውልዶች ላይ ጫና ያለው ውል ሊዋዋል አይገባውም።</u>*** *እኛም መብቱም ሥልጣኑም የለንም።" አሉ ሲሉ፦ አስፈቅጄ ነገሩን ምን እንዳመጣውና ርሳቸውም ለምን እንደተደነቁ ጠየቅኋቸው፦ ፈገግ ብለው " የምወድድህ የነገርሁህስ ለዚህ አይደል?" ብለው፦*
*"መንሰኤው አንዳንድ ኃያላን መንግሥታት ጫና ሊያደርጉባቸው መሞከራቸው ሲኾን፦ ያስገረመኝም ጃንሆይ* ***<u>' እኛም መብቱም ሥልጣኑም የለንም"</u>*** *ማለታቸው ነው።" አሉና አኹንም በፈገግታ ሳትጠይቀኝ ልቀጥላ! መቼም አትተወኝ። " ጃንሆይ በጣም ዐዋቂ ስለኾኑ መብትና ግዴታቸውን ማወቃቸው አይደለም ያስደነቀኝ። ለሌሎቻችን 'መብትም ሥልጣንም የለን!' ብለው መናገራቸው ነው።አሉ ታዲይ የአኹኑን ጉዶች በዚህ ዓይነት ለትውልድ ተቆርቋሪነት ማማት ይቻላል?*

*ኮሎኔል መንግሥስቱ በግብታዊነት " አንዱን ብርጭቆ ውሀችንን በጠርሙስ ቤንዚን እንለውጣለን።" አለ ከዚህ ጋር በተተያያዝ ይኹን አይኹን አላስታውስም የግብጹ ፕሬዜዳንት ሳዳት " እኛ የምንፈራው ወደ አሜሪካ ሲዘምት (መንግሥቱ) እግረ-መንገዱን እንዳይዳምጠን ነው።" ብሎ ቀለደ። ወደ አሜሪካ ማለቱ ፕሬዜዳንት ካርተርን " የኦቾሊኒ ገበሬ!" እያለ ይዘልፍ ስለነበር ነው።*

*እንግዲህ ኢትዮጵያ፦ እስከ ሕ.ወ.ሃ.ትግራይ ድረስ ከግብጽም ኾነ ወይም ከሱዳን ጋር የተዋዋለችው ነገር አለመኖሩን ኹላችንም ልናሰምርበት ይገባል። በአንዳንድ መድረኮች ላይ 'እስካኹን ባሉት/ያሉት ውሎች' ብለው ይጀምሩና የአድማጮቻቸውን ቅስም ከሰበሩ በኋላ በንግግራቸው መኻከል 'ኢትዮጵያ ግን ከአጼ ምኒልክ ውል በስተቀር የፈረመችው የለም።' ሲሉ ኃይለ-ቃሉን፦ ብሎም ዕውነታውን ያዳክሙታል። ቅደም-ተከተሉን መለወጥና የእምዬ ምኒልክን ውል በቁሙ እንኳን አስቀድሞ ማስቀመጥ አገር ወዳድነት ብቻ ሳይኾን ታሪክ አክባሪነትም ነው።*

## *የነመለስ ዓላማና ግዴታዎች፦*

*ዓላማቸው*

*ትግራይን ገንጥለው ከኤርትራ ጋር በማዋሀድ "ታላቋ ትግራይ"ን ለመፍጠር ነው።የዚህም ጽንሰ-ሃሳብ ምንጯ እንግሊዝ ናት። በምሥራቅም ኦጋዴንን አስገንጥላ " ታላቋ ሶማሊያ! " እንድትፈጠር በሶማሌዎች ላይ ባሠረጸችው ጽንሰ-ሃሳብ በዚያ በኩል ያለብንን ችግር መግለጽ አያሻም።*

*ግዳጆቻቸው፦*

- *<u>ኤርትራን ማስገንጠል</u>*
  *ይህን ሲያደርጉ ኤርትራ ከቀድሞውም ከኢጣሊያን ስትገላገል "እናት ኢትዮጵያ ወይ ሞት!" ብለው በታገሉላት ልጆችዋ፦ በቀኃሥና ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ በሌሎቹም ልፋት ልትዋሀድ ስትችል በብዙ ተንኮል በአህጉራችን ተሰምቶ የማይታወቀውን "ፌደሬሽን" የሚል ችግር ሸነቀሩብን። ዋናው ነገር ለእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር ሃላፊነቱ የተጣለበት ጸጥታ ጉባኤው በአባላቱ የግል ጥቅም ማስቀደም፦ በዚህም (በፌደሬሽን) ቢኾን መስማማት አቅቶት የተመ ጠቅላላ ጉባኤ ከኢትዮጵያ ትቀላቀል ብሎ ሲወስን ' ኢትዮጵያ ትልቅ አገር እንደመኾንዋ የባሕር በር ያስፈልጋታል። በታሪክም በሕግም ቢያንስ አሰብ የርስዋ በር መኾን አለበት። ይህ ካልኾነ ለአካባቢው ጸጥታ መደፍረስ ጠንቅ ይኾናል።' ያለውን ጸጥታ ጉባኤ የተባሉት የጠቅላላ ጉባኤውን አርቆ-አሳቢነትና ታሪክ አክባሪነት እንዲሁም ለአካባቢው ሕዝብ ሰላም ሲል የወሰነውን ሽሮ ኢትዮጵያን ያለ በር አስቀራት። ማ መንግሥት ኾኖ ይከራከርላት? ለዚያስ ትሂድ ብሎ የወተወተው መንግሥት ተብዬው አይደል?*
  *ይህን ግዳጃቸውን ተወጡት!*

- *ኢትዮጵያን በጎሳና በቋንቋ ( ብሔር) መከፋፈል።* የዚህ ሀሳብ አመንጪ ባሮን ሮማን ፕሮችሀዝካ የሚባል የኦስትሪያ ናዚ በ ፴ ዎቹ ኢትዮጵያ ስለነበር ቀኃሥ፦ ዳግማዊ ምኒልክ በስማቸው የተጠራውን ትምሕርት ቤት ሲከፍቱ አስተማሪዎች ከነጮች አገር ማግኘት አቅቷቸው ከግብጽ (በቤተ-ክርስቲያን አማካይነት) በእጅግ ውድ ደመወዝ ማስመጣት መቻላቸውን በመረዳት በውጪ ጉዳይ ሚንስትራቸው፦ በብላቴን ጌታ ኀሩይ፦ አማካይነት የጃፓንን ንጉሠ ነገሥትናመንግስትን አሳምነው የኹለቱ ጥንታውያን የዘውድ አገሮች በጋብቻ ተሳስረው እንዲረዳዱ መስማማታቸውን ( እንግሊዝ ያስጨነገፈችውን) እና በነጭ አለመደፈሯን አይቶ 'ኢትዮጵያ ለነጭ ጥቅም ጠንቅ ነች ብሎ ፈርጆ " ኢትዮጵያ የባሩድ በርሜል!" በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፎ፦ መጽሐፉም በብዙሐን የአውሮፓ ቋንቋዎች ተተርጉሞ መድሀኒቱ እላይ እንደ ተጠቀሰው ኢትዮጵያን በጎሳ (ብሔር) መበታተን ነው ባለው መሠረት ሕ.ወ.ሃ.ት (ለ)በፈረንጅ ታዛዥነት ኢትዮጵያን መበታተኚያ እንዲኾን ባዘጋጁለት ሕገ-መንግሥት ተብዬውን ባገር ልጆች እንደተረቀቀ አስመስለው የሕዝብ ውክልና ባልነበራቸው ስብስቦች ኢትዮጵያን በክልሎች ከፍለው የክልሎቹም ገዥዎች በ"ፕሬዜዳንትነት" ታውቀው ነበር።

በግልፍተኝነት ሕዝቡ ቢቃወመው ወዲያዉኑ ኤርትራን እንደገነጠሉ ትግራይንም ገንጥለው ሌሎቹንም ለመበታተን ነበር።

የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆች በትዕግስት ዝም ሲሏቸው፦ ወዲያው መበታተኑን ትተው መቦጥቦጡን ቢቀጥሉም የመከፋፈያ ሥራቸውን አላቆሙም ነበር። የኢትዮጵያ አምላክ ቅንጅትን ሲያስነሳና ቅንጅትም "አንድነትን" አንግቦ ገዥዎቹን ድባቅ ሲመታቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንድነቱ ያለውን ክብርና ፍቅር አይተው ንግዳቸውን ለወጥ በማድረግ፦

## ብሔር ብሔረ-ሰቦች፣
## ኹሉም የኢትዮጵያ ልጆች !

እያሉ ዘፈኑ - አዘፈኑ፦ ጨፈሩ አስጨፈሩ። ሕዝቡን "ለአንድነት የቆምን ነን" ብለው አማልለው እሴቱን ኹሉ እየቦጠቦጡ አስቦጠቦጡ።

## - ሰንደቅ አላማችንን ማስቀረት፦

ሰንደቅ ዓላማችን ለአፍሪካ ብቻ ሳይኾን በካሪቢያንና ተወላጆቻቸውም ባሉባቸው አሜሪካንና አውሮፓ ኹሉ የገነነ በመኾኑ፦ ይበልጥም አፍሪካ ሲዋሀድ የሰንደቅ ዓላማ ችግር የማያመጣ በመኾኑ እንዲያውም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ የአፍሪካ ማድረጉ ጥርጣሬ ባለመኖሩ፦ በታዘዙት መሠረት ሰንደቅ ዓላማችንን በማዋረድና በማራከስ ብሎም "የጭቆና ምልክት" እያሉ በማስጠላት ለማስቀረት ጣሩ፦ እዚህ ላይ በቅርቡ ያለፉትን አባታችንን ሱልጣን ቢትወደድ አሊሚራህን በአገር ወዳድነትቸው፤ በታሪክ አክባሪነታቸው በያለንበት " በነፍስ ይማር በክብር! " እናስታውሳቸው፣

- ይበልጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ረገድ የማይታለል የማይገዛ ኾኖ ቢያስቸግር ያደረገውን የማያውቅ የለም። ጣሊያን እንኳን ኤርትራን ስትገዛ ሕዝቡ ለዐውደ-ዓመቱ፦ለሠርጉና ለሞቱ በአረንጓዴ ብጫ ቀይ ሰንደቅ ኣላምው እንዲያከብር **<u>ያከበረውን</u>** ከኢጣሊያን ብሰው አስቀማጮቻቸውን ለማስደሰትና ታዛዥነታቸውን ለማረጋገጥ የኢትዮጵያን ሕዝብ አሳዘኑት አዋረዱትም።

- *<u>የማዕድን ሃብት፦</u>*

ተደፍሮ የማያውቀውን የከርሰ-ምድር ሀብቷን በታዘዙት መሠረት፣ በዘበዙት አስበዘበዙት። ቀ.ኃ.ሥ. መጀመሪያ አሜርካንን የጎበኙ ጊዜ፤ ጋዜጠኞች "አገርዎ ብዙ ማዕድን አላት ይባላል። ታዲያ ለምን አይወጣም?" ቢባሉ "ዕውነት ነው ግን ልጆችዋን ትጠብቃለች አሉ።"

- የሕዝቡ ዝምታ የልብ ልብ ሰጥቷቸው ምን ያላደረጉት አለ? የተቀደሰውን መሬትዋን ገምሰው በሽፍትነት ጊዜ ለረዷቸው ሱዳኖች ሰጡ፦

- *አንድ ጨዋታ ላቅምሳችሁ። የቤት ሠራተኛ ከተኛችበት ጌታዋ ሂዶ አንዳንድ ነገር ሲጀምር “ ጉዱን አያለሁ ብዬ ዙም አልሁ…”
  አለች እንደተባለችው የኢትዮጵያ ሕዝብም አኹንም “ ዙም !” በማለቱ ራሱ እየተራበ ለም መሬቱ ኹሉ የስጦታ ያህል እየተቸበቸበ ነው።*
- *ውዘተ*

# *አኹንስ ሕ.ወ.ሃ.ትግራይ ምን ቀረው?*

*ፈቃዱ ይኹንና በኹለተኛው ክፍል ይኸንንና ተመሳሳይ ጉዳዮችን
ለማቅረብ ርኖክራለሁ*